www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.58
ADDIS ABABA 19th April, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፪/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ገጽ…፲፩ሺ፪፻፳፱

## Content

Proclamation No.1132/2019

Prevention and Suppression of the Financing of the Proliferation of Weapons of Mass Destruction Proclamation ……..…………………..…....Page 11229

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፪/፪ሺ፲፩

**<u>የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ</u>**

የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜት እና ይህንኑ በገንዘብ መደገፍ ዓለም አቀፍ የደህንነት ስጋት በመሆኑ፤ ሁሉም ሃገራት ይህን ለመከላከል፣ ለመግታት እና ለመቆጣጠር በሚደረጉ ሉላዊ የትብብር ማዕቀፎች በጋራ እና በትብብር እንዲሰሩ በማስገደዱ፤

ኢትዮጵያ የጅምላ ጨራሽ መሳሪያዎች ብዜትን ከመከላከልና ከመቆጣጠር ጋር ተዛማጅነት ያላቸዉ የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ያፀደቀች በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ውስጥ ሊካሄዱ ወይም ሊያልፉ የሚችሉ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን የሚደግፉ ማናቸውንም ተግባራት መከላከልና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

እያንዳንዱ ሀገር በስምምነቶቹ የተጣሉበትን ኃላፊነቶች ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ስለሚጠበቅበት እና ለዚህም አተገባበር ሃገራዊ ህግ ማዉጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO.1132/2019

**<u>A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PREVENTION AND SUPPRESSION OF FINANCING THE PROLIFERATION OF WEAPON OF MASS DESTRUCTION</u>**

WHEREAS, the Proliferation of Weapons of Mass Destruction and its Financing have become a global security problem, making it necessary for all states to collaborate in global initiatives to prevent, suppress and disrupt it;

WHEREAS, Ethiopia has ratified the Conventions and Treaty on the Prohibition of the Development, Production, Use of Weapons of Mass Destruction and their Proliferation;

WHEREAS, it is necessary to prevent and tackle all activities in support of the proliferation of weapons of mass destruction that might take place in or through Ethiopia;

WHEREAS, it is agreed that each state party must adopt the necessary measures to implement its obligations under the conventions and treaty, and to this effect the issuance of a national law has become necessary;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby Proclaimed as follows.

www.chilot.me



## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ መደገፍን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፪/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች" ማለት ሀገራችን ባፀደቀቻቸው የኒኩሊየር፣ የስነ-ህይወት ወይም የኬሚካል ህጎች ላይ በተመለከተው አግባብ በሥነ-ምሕዳር ወይም በመሰረተ-ልማት፤ ወይም ከፍተኛ ቁጥር ባለው ሕዝብ፣ እንስሳት ወይም ነፍሳት ላይ ከፍተኛ ጉዳትን፣ እልቂትን ወይም ውድመትን የሚያስከትል የኒኩሊየር፣ የስነ-ሕይወት ወይም የኬሚካል ጦር መሳሪያ ሲሆን የእነዚህን ጦር መሣሪያዎች ተሸካሚ ይጨምራል፤

፪/ "ተሸካሚ" ማለት ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን ተሸክሞ ለማሸጋገር ከተለያዩ ግብዓቶች ተገጣጥሞ ሊሰራ የሚችል ማናቸውም መሣሪያ ሲሆን መንኮራኩር፣ የተወንጫፊ ሚሳኤል ሥርዓት፣ የልኬት መንኮራኩር፣ ሰው አልባ የአየር ሰረገላ፣ ባሌስቲክ ሚሳኤልን እንዲሁም ጅምላ ጨራሽ ጦር መሣሪያን ተሸክሞ ሊያሸጋግር የሚችል ማናቸውንም ነገር ይጨምራል፤

፫/ "የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ እቅድ" ማለት ለጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ብዜት የተዘጋጀ እቅድ ወይም መርሐ-ግብር ነው፤

፬/ "ብዜት" ማለት ከአገር አቀፍ ሕጎች እና ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተጻራሪ ጅምላ ጨራሽ ጦር መሣሪያዎችን ማምረት፣ መቀበል፣ መያዝ፣ ማበልፀግ፣ ወደ ውጭ አገር መላክ፣ መጫን፣ ማራገፍ፣ መደለል፣ ማጓጓዝ፣ ማስተላለፍ፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም ነው፡፡

፭/ "የገንዘብ ድጋፍ" ማለት ጅምላ ጨራሽ የጦር መሳሪያ ብዜትን በመደገፍ ሀሳብ ወይም የመደገፍ ውጤት እንዲኖረው በማሰብ የገንዘብ፣ የፋይናንስ አገልግሎት ወይም ማናቸውንም ሀብት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለግለሰብ፣ ለድርጅት ወይም ለሀገር መስጠት ነው፡፡

## PART ONE
## GENEAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "Prevention and Suppression of the Financing of the Proliferation of Weapons of Mass Destruction Proclamation No.1132/2019".

### 2. Definition

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "Weapons of Mass Destruction" means nuclear, biological, or chemical weapons that are capable of a high order of destruction and/or of being used in such a manner as to kill, harm, infect or destroy large numbers of people or animals or to cause significant environmental or infrastructural damage as are defined in the nuclear, biological, or chemical weapons law that Ethiopia approved as well as their delivery system.

2/ "delivery system" means any combination of instruments that is capable of delivering Weapons of Mass Destruction such as a rocket, a ballistic missile system, a sounding rocket or unmanned air vehicle, cruise missile, and any other things.

3/ "Weapons" of Mass Destruction program" means a plan or a program for proliferation of weapons of mass destruction.

4/ "Proliferation" means the manufacture, acquisition, possession, development, export, shipment, brokering, transport, transfer, stockpiling or use of weapons of mass destruction in contravention of national laws and international agreements ratified by Ethiopia.

5/ "Financial support" means the act of providing funds, any resource or financial services to an individual, an entity or a state with the intention or having the effect of directly or indirectly aiding the proliferation of weapons of mass destruction.

፮/ "የፋይናንስ ተቋም" ማለት ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የፖስታ ቁጠባ ተቋም፣ የሐዋላ ድርጅት፣ የውጭ ገንዘብ ምንዛሬ ተቋም ወይም ብሔራዊ ባንክ አግባብ ባለው የሕግ ማዕቀፍ መሠረት የፋይናንስ ተቋም ብሎ የሚሰይመው ማናቸውም ሌላ ተቋም ነው፤

፯/ "የተሰየሙ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የንግድና የሙያ ሥራዎች" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ) የሪል ስቴት ወኪሎችና ደላሎች፤

ለ) የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶች ነጋዴዎች፤

ሐ) የሚከተሉትን ለደንበኞቻቸው የሚያዘጋጁ፣ የሚፈጽሙ ወይም የሚያከናውኑ ጠበቆች፣ ኖታሪዎች እና ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች፡-

(፩) ሪል ስቴት መግዛትና መሸጥ፤

(፪) የደንበኛቸውን ገንዘብ፣ ዋስትናዎችን ወይም ሌላ ሐብትን ማስተዳደር፤

(፫) የባንክ፣ የቁጠባ ወይም የዋስትና ሂሳቦችን ማስተዳደር፤

(፬) ኩባንያ ለመመስረት፣ ለማካሄድ ወይም ለማስተዳደር የሚደረጉ መዋጮዎችን ማስተባበርና ማደራጀት፤ ወይም

(፭) የሕግ ሰዉነት ያላቸውን ተቋማት መመስረት፣ ሥራቸውን ማስኬድ ወይም ማስተዳደር እንዲሁም የንግድ ተቋማትን መግዛትና መሸጥ፤

መ) ራሳቸዉን ችለዉ የተቋቋሙ የሂሳብ ባለሙያዎች፤ በግል፣ በጋራና በሙያ ማሕበር ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች፣

ሠ) የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች፤

ረ) የጥናትና ቴክኖሎጂ ተቋማት፤

ሰ) አምራቾች፤

ሸ) ደላሎች፤እና

በ) በማዕከሉ የሚሰየሙ ሌሎች የንግድና የሙያ ሥራዎች፡፡

፰/ "ማዕከል" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፸፩/፪ሺ፪ የተቋቋመዉ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል ነው፤

፱/ "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

6/ "Financial institution" means a bank, an insurance company, a micro finance institution, postal savings, money transfer institution, foreign exchange bureaus or any other institution designated as Financial institution by the National Bank pursuant to the relevant legal framework;

7/ "Designated non-financial businesses and professions" include:

a) Real estate agents and brokers;

b) Dealers in precious metals or precious stones;

c) Lawyers, notaries and other independent legal professionals when they prepare for, carry out or engage in transactions for their clients concerning:

(1) buying and selling of real estate;

(2) managing of client's money, securities and other assets;

(3) management of bank, savings or securities accounts;

(4) organization of contributions for the creation, operation or management of companies; or

(5) creation, operation or management of legal persons and buying and selling of business entities;

d) Independent accountants including sole practitioners, partners or professionals within the professional firms;

e) Transportation service providers;

f) Research and technology institutions;

g) Manufacturers;

h) Brokers; and

i) Others businesses and professions that may designate by the Centre.

8/ "Centre" means the Financial Intelligence Centre established by the Council of Ministers Regulation No 171/2009.

9) 'Person' means a natural person or a juridical person.

www.chilot.me



፲/ በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

፩/ ይህ አዋጅ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ የመደገፍን ተግባር መከላከል በተመለከተ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ ይህ አዋጅ ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን ከማባዛት ውጭ ለሆነ ዓላማና ተግባር የሚውሉ የኒኩሊየር፣ ኬሚካል እና ስነ-ሕይወታዊ ቁሶችን እና/ወይም የእነዚህን ጦር መሣሪያዎች ተሸካሚን በተመለከተ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው መንግስት የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ መደገፍ በተመለከተ ያሉበትን ግዴታዎች ከመፈጸም አንጻር የሚወሰዱ አስፈላጊ እርምጃዎችን የሚከለክል ሆኖ አይተረጎምም፡፡

## ክፍል ሁለት
## አስፈፃሚ አካላት

**፬. የብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋም**

፩/ "የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ፀረ-ብዜት ብሔራዊ ኮሚቴ" ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ፤ በዚህ አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል፡፡

፪/ የኮሚቴው ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡

፫/ የሰላም ሚኒስቴር የኮሚቴው ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፡፡

፬/ ሴክሬታሪያቱ የኮሚቴውን በጀት የማዘጋጀት እንዲሁም የኮሚቴውን ወጪዎች እንደ አግባብነቱ ፈሰስ በማድረግ የመሸፈን ተግባርና ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

**፭. የኮሚቴው አባላት**

የኮሚቴው ሰብሳቢ የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩/ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣

፪/ የጠቅላይ ዐቃቤ-ሕግ፣

፫/ የመከላከያ ሚኒስቴር፣

፬/ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣

**10)** Any expression in the masculine gender includes the feminine

**3. Scope of Application**

1/ This Proclamation applies to activities done to protect the financial support of the proliferation of weapons of mass destruction.

2/ This proclamation doesn't apply to activities made for the purpose of civil use and /or delivery of nuclear, chemical and biological substances.

3/ Nothing in Sub-article (2) of this Article shall be construed to preclude the government from taking the necessary measures to implement obligation against proliferation of weapons of mass destruction financial support.

## PART Two
## THE EXECUTIVE ORGANS

**4. ESTABLISHMENT OF NATIONAL COMMITTEE**

1) A National Committee, herein after called the "Committee" on the Non-Proliferation of Weapons of Mass Destruction is here by established. e

2) The Committee is accountable to the Prime Minister.

3) The Ministry of Peace serves as a secretariat to the Committee.

4) The Secretariat is responsible for preparing the budget and procuring resources to cover the expense of the committee.

**5. MEMBERS OF THE COMMITTEE**

The Committee shall be chaired by the minister of ministry of peace and shall comprise the following members:

1/ The Ministry of Foreign Affairs;

2/ The Attorney General;

3/ The Ministry of defence;

4/ The National Intelligence and Security Service;

www.chilot.me



፭/ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣

፮/ የጤና ሚኒስቴር፣

፯/ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣

፰/ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣

፱/ የገንዘብ ሚኒስቴር፣

፲/ የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል፤

፲፩/ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ፤

፲፪/ብሔራዊ ባንክ፤

፲፫/ሌሎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ አባል እንዲሆኑ የሚሰየሙ የመንግስት አካላት፡፡

**፮. የኮሚቴው ስልጣንና ተግባራት**

ኮሚቴው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ በኢትዮጵያ ወይም ኢትዮጵያን እንደመሸጋገሪያ በመጠቀም የሚፈፀም የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ መደገፍ በተመለከተ ስላለው ሁኔታ በመገምገም ድርጊቱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን እና አመራሮችን የመስጠት፣ መመሪያዎችን የማውጣት፤

፪/ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ ከመደገፍ ጋር ተያይዞ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የሚወሰኑ ቅጣቶችና ማዕቀቦች በአገር ውስጥ መፈፀማቸውን የመከታተል፤

፫/ በአገር ውስጥም ሆነ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚጣሉ ቅጣቶችና ማዕቀቦች በአግባቡ እና በጊዜ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችል ክትትል እና ድጋፍ የመስጠት፤

፬/ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ የመደገፍ ስጋት ደረጃን በተመለከተ በግብረ ኃይሉ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ተቋማት የተሰራውን የዳሰሳ ጥናት ማፅደቅ እና ለተጨማሪ እርምጃዎች አቅጣጫ የመስጠት፤

፭/ የኒኩሊየር፣ የኬሚካል እና የስነ-ሕይወት ንጥረ ነገሮች ልየታዎች እና አጠቃቀሞች በተመለከተ ለብሔራዊ ግብረ ኃይሉ መመሪያ መስጠት፤

፮/ የጅምላ ጨራሽ የጦር መሳሪያዎች ብዜትን በተመለከተ ከፍተኛ ስጋት ናቸው የሚባሉ ግብይቶችን እና ደንበኞችን ዝርዝር ማዘጋጀትና ለፋይናንስ ተቋማትና ለተሰየሙ ፋይናንስ ያልሆኑ ተቋማት መመሪያዎችን ማዘጋጀት፤

5/ The Federal Police Commission,;

6/ The Ministry of Health;

7/ The Ministry of Trade and Industry;

8/ The Ministry of Innovation and Technology;

9/ The Ministry of Finance;

10/ the Finance Security Information Center;

11/ the Information Network Security Agency;

12/ National Bank;

13/ Other Government Organs designated by the Prime Minister.

**6. Powers and responsibility of the Committee**

The Committee shall have the following powers and responsibilities:-

1/ Provide direction and leadership, issue Directives in the evaluation of the risk of financial support for proliferation of weapons of mass destruction made in Ethiopia or by using Ethiopia as transit;

2/ Oversee the domestic implementation of punishments and sanctions of the United Nations Security Council in relation to financing of proliferation of weapons of mass destruction;

3/ Provide guidance and support for the proper and the timely implementation of domestic and United Nations sanctions and penalities;

4/ Approve the assessment of the risk of financing the proliferation of weapons of mass destruction conducted by the National Task Force or by other appropriate organs and provide directions for further actions;

5/ Provide directions to the National Task Force on the differentiation and use of of Nuclear, chemical and biological substances;

6/ Prepare a list of high risk transactions and customers and prepare guidelines for financial institutions and designated non-financial businesses in relation to proliferation of weapons of mass destruction;

www.chilot.me



፯/ እንደ አስፈላጊነቱ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ ብሄራዊ ግብረ ሃይሎችን የማቋቋም::

**፯. የኮሚቴው ስብሰባ**

፩/ ኮሚቴው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባዎች ያካሂዳል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ላይ የተመለከተው ቢኖርም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊቀመንበሩ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫/ ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ኮሚቴ ይሆናል፡፡

፬/ የኮሚቴው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ድምፅ እኩል በእኩል በተከፈለ ጊዜ ሊቀመንበሩ የደገፈው ይፀድቃል፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የአሰራር ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን በገንዘብ መደገፍን ስለመከላከል፣ መግታትና መቆጣጠር

**፰. ክልከላዎች**

ማንኛውም ሰው የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን ወይም እቅድን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ በተሟላ ሁኔታም ይሁን በከፊል በገንዘብ ድጋፍ፣ በቁሳቁስ፣ በንብረት፣ በኢኮኖሚያዊ ኃብቶች፣ በገንዘብ ነክ አገልግሎት ወይም በቴክኒካዊና ሙያዊ አስተዋፅዖ መደገፍ የተከለከለ ነው፤

**፱. ኢላማ የገንዘብና የንብረት ቁጥጥሮችና ማዕቀቦች**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔ የተጠቀሰን ሰው ሂሳብ ወይም ንብረት እና ማናቸውም ዋጋ ያላቸው ሃብቶቹን የሚያግድ፤ እንዲሁም ለእርሱ ወይም ስለ እርሱ በሚሰሩ ወይም በእርሱ ታዘው ለሚሰሩ ሰዎች ተደራሽ እንዳይሆኑ የሚከለክል ውሳኔን ያሳልፋል፡፡

7/ Establish National Task Force as appropriate for carrying out tasks necessary for the implementation of this proclamation.

**7. Meeting of the Committee**

1/ The committee shall hold regular meetings twice a year.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub article 1of this Article the chair person may call extraordinary meetings as it become necessary.

3/ The presence of more than half of the members of the committee constitutes a quorum.

4/ Decisions of the Committee shall be passed by majority vote, provided that the chairperson shall have a casting vote in the event of a tie.

5/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Committee may adopt its own rules of procedure.

## PART THREE

## PREVENTION, SUPRESSION AND DESRUPTION OF THE FINANCIAL SUPPORT OF PROLIFERATION OF WEAPONS OF MASS DESTRUCTION

**8. Prohibition**

No person may provide finance, other assets, economic resources, financial services, or technical or professional support for directly or indirectly in whole or in part, the proliferation of weapons of mass destruction or their programs.

**9. Targeted Financial and Asset Control and Sanctions**

1/ The Council of Ministers shall order the freezing of any funds or other assets and economic resources of a person designated by United Nation Security Council Resolution, and prohibit funds, other assets, and economic resources from being made available to or for the benefit of the person as well as to or for the benefit of those acting on behalf or at the direction of such person.

www.chilot.me



፪/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለፀው መሰረት ሲወስን የሰጠው እግድ ወይም ክልከላ ስለሚፈፀምበት ዝርዝር ሁኔታ እና ክልከላው ወይም እግዱ የሚቆይበትንም ጊዜ ወስኖ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤ ትዕዛዙም ሰፊ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ እንዲታተም ያደርጋል፡፡

፫/ ስሙ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በጅምላ ጨራሽ መሳሪያ ብዜት ድርጊት የተጠቀሰ ሰው እንዲሰረዝ በቀጥታ ወይም በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ሊያመለክት ይችላል:: የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ስሙ የተጠቀሰን ሰው ካልሰረዘው በስተቀር በሀገር ደረጃ መሰረዝ አይቻልም፡፡

፬/ ማዕከሉ ስሙ የተጠቀሰን ወይም የተሰረዘን ሰው በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ለፋይናንስ ተቋማትና ለተሰየሙ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የንግድና የሙያ ሥራዎች አካላት በደብዳቤ፣ በኢሜል ወይም በሌላ መገናኛ መንገድ ማሳወቅ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ትዕዛዝ ሰፊ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት በ፳፬ ሰዓት ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት እና የተሰየሙ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የንግድና የሙያ ሥራዎችን ጨምሮ ማናቸውም ሰዎች የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፡-

ሀ) ሌላ ማስታወቂያ እንዲደርሳቸው ሳያስፈልግ የሚከተሉትን አግደው መያዝ አለባቸው፡-

(፩) በውሳኔው በተጠቀሱ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በሙሉም ሆነ በከፊል፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በባለቤትነት ወይም በቁጥጥራቸው ስር ያሉ፣ ገንዘብ፣ ሌላ ንብረት እና ኃብታቸውን ሁሉ አግደው መያዝ አለባቸው፤

(፪) በውሳኔው የተጠቀሱ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በባለቤትነት ወይም በቁጥጥራቸው፤ በሙሉም ሆነ በከፊል፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከያዙት ገንዘብ፣ ሌላ ንብረት ወይም ኃብቶች የመነጨ ገንዘብ፣ ሌላ ንብረት ወይም ኃብቶችን ሁሉ አግደው መያዝ አለባቸው፤

(፫) በተመረጡት ሰዎች ምትክ የሚሰሩ ወይም በእነርሱ ትዕዛዝ የሚሰሩ ሰዎችን ገንዘብ፣ ሌላ ንብረት ወይም ኃብቶች የመነጨ ገንዘብ፡፡

2/ Where the Council of Ministers decides as per Sub-article (1) of this Article, it shall define the duration, terms and conditions applicable to the freezing or prohibition, and cause its order to be published in newspaper having wide circulation.

3/ A person deleted for proliferation of weapons of mass destruction by United Nation Security Council may apply for delisting either through the Ministry of Foreign Affairs or via direct appeal to the United Nation Security Council. Domestic delisting cannot be granted so long as a person's deletion remains in place at the United Nation Security Council level.

4/ The centre shall communicate both deletion and delisting of persons to financial institutions and designated non-financial and business professionals by letter or through email or other means of communication within 24 hours.

5/ following the publication of the decision of the Council of Minister in newspaper having wide circulation as per Sub article 2 of this Article, all persons including financial institutions and designated non-financial businesses and professions, shall within 24 hours:

a) without seeking other notice have to freeze and hold the followings;

(1) funds, other assets and economic resources owned or controlled wholly or partially; directly or indirectly; by the designated person; and organizations;

(2) Funds, other assets and economic resources derived or generated from funds, other assets, or economic resources owned or controlled, wholly or partially; directly or indirectly; by the designated persons or organizations;

(3) Funds, other assets and economic resources generated from funds of persons acting on behalf of or at the direction of designated person.

www.chilot.me



(ለ) ተጓዳኝ ግብይቶችን እንዲሁም በዚህ አዋጅ በተደነገገው አግባብ አግደው ስለያዙት ገንዘብ ፣ ሌላ ንብረት ወይም ኃብት ወይም ስለወሰዱት ሌላ እርምጃ ወዲያውኑ ለማዕከሉ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

(ሐ) በማዕከሉ ካልተፈቀደ በስተቀር የታገዱ ገንዘቦችን፣ ሌላ ንብረት ወይም ኃብቶችን መስጠት ወይም መልቀቅ የለባቸውም፡፡

፮/ ማዕከሉ ይህን አዋጅ መሰረት አድርጎ በሚወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በዝርዝር በሚወሰነው መሰረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተዘረዘሩት ላይ እንዲለቀቁ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፯/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለፀው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ተፈፃሚ ሲደረግ የባለቅን ልቦና ሦሥተኛ ወገን ጥቅም መገናዘብ ይኖርበታል፡፡

፰/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በተሰጠ ውሳኔ መነሻነት በሁኔታው አጋጣሚ ሳይታሰብ ጥቅማቸው የተነካባቸው ሰዎች በውሳኔው የተጠቀሱት ትክክለኛ ሰዎች እነሱ አለመሆናቸውን ከማስረጃ ጋር አያይዘው በመጥቀስ አቤቱታቸውን ለማዕከሉ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

፱/ ማዕከሉ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተሰጠው ውሳኔ የሚመለከታቸው ትክክለኛ ሰዎች እነሱ አለመሆናቸውን ጠቅሶ ማረጋገጫ ሲሰጥ በውሳኔው መነሻነት ማረጋገጫ የተሰጣቸው የእነዚህን ሰዎች ጥቅሞች የተመለከቱ የማገድና ክልከላ እርምጃዎች ቀሪ ይሆናሉ፡፡

## ፲. <u>እርምጃ ተኮር መረጃ ስለመስጠት እና ማዕቀቦች</u>

፩/ የፋይናንስ ተቋማት እና የተሰየሙ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የንግድ እና የሙያ ተቋማትና ሥራዎች ከፍተኛ የስጋት ተጋላጭነት ያላቸው ደንበኞችን እና ግብይቶችን የመለየት፣ የእነዚህን ደንበኞች እና ግብይቶች እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት ልዩ የክትትል ስርዓት የመዘርጋት እና ተገቢ የሆነ የክትትል እርምት እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ የፋይናንስ ተቋማት እና የተሰየሙ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የንግድ እና የሙያ ተቋማትና ሥራዎች ከፍተኛ የስጋት ተጋላጭነት ያላቸው ደንበኞችን እና ግብይቶችን ሲለዩ የሚከተሉትን ማገናዘብ ይኖርባቸዋል፦

b) Report immediately to the Centre any funds, economic resources and assets frozen and actions taken in accordance with the provisions of this proclamation, including any attempted transactions.

c) Refrain from making available or releasing frozen funds, other assets, and economic resources without specific authorization by the Centre

6/ In accordance with the specification that shall be provided under the regulation to enforce this proclamation, the Centre may give authorization for release to those provided under Article 11 of this Proclamation.

7/ The interests of *bona fide* third party shall be taken into consideration when implementing the Council of Ministers decision taken pursuant to Sub-article (1) and (2) of this Article .

8/ Persons inadvertently affected by a decision taken pursuant to Sub-article (1) and (2) of this Article may make application to the Centre with proof that they are not the persons listed in the decision.

9/ The asset freezing and prohibition measures taken pursuant to Sub-article (1) and (2) of this Article shall be terminated with respect to those persons up on confirmation by the Centre to have been mistakenly identified.

## 10. <u>Activity Based Reporting and Sanction</u>

1/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions should identify high-risk customers and transactions, apply enhanced scrutiny to such customers and transactions, and take appropriate follow-up action.

2/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions should consider the following information in identifying high-risk customers and transactions:

www.chilot.me



ሀ) በማዕከሉ የሚወጡ ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን በገንዘብ ስለመደገፍ አመላካች የሆኑ አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን፤

ለ) በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እንዲሁም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መደገፍን ከመከላከልና ከመቆጣጠር ጋር ተያይዘው ካሉ ግዴታዎች አንጻር የተሰበሰቡ ስለደንበኞች እና ስለግብይቶች የተመለከቱ መረጃዎችን፡፡

፫/ የፋይናንስ ተቋማት እና የተሰየሙ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የንግድ እና የሙያ ተቋማትና ሥራዎች ከጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በሚጠረጠሩ ደንበኞች እና ግብይቶች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለማስቻል ወዲያውኑ ለማዕከሉ ማስታወቅ አለባቸው፡፡

፬/ ማዕከሉ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት እንዲያውቀው ከተደረገው ግብይት ጋር የተያያዙ ገንዘብ፣ ሌላ ንብረት እና ኃብትን ከአስር ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ታግዶ እንዲያዝ ለማዘዝ ይችላል፤ ሆኖም ይህን እርምጃ ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ-ሕግ ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት፡፡

፭/ የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ-ሕግ አግባብነቱን በመመርመር የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ እንዲፀና እና እንዲራዘም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያመለክታል፡፡

## ፲፩. <u>ከእግድ ነፃ ሊደረጉ ስለሚችሉ ገንዘቦች፣ ንብረቶች እና ኃብቶች</u>

የሚከተሉት ገንዘቦች፣ ንብረቶችና ኃብቶች ከእግድ ነፃ ሊደረጉ ይችላሉ፡-

፩/ በኪራይ ወይም በዋስትና ክፍያዎች፣ በደመወዝ፣ በግብርና በቀረጥ፣ በመድህን አረቦን፣ በሕዝባዊ አገልግሎት ክፍያዎች ወይም በሕግ ሙያ አገልግሎት ክፍያዎች ላይ፤

፪/ ሦሥተኛ ወገኖች በቅን ልቦና በያዟቸው ገንዘቦች፣ ንብረቶች ወይም ሌሎች ኃብቶች ላይ፤

፫/ በንብረት አስተዳዳሪ እና በሂሳብ አጣሪ የሙያ ክፍያዎች ላይ፤

a) relevant information provided by the Centre on indicators of the financing of the proliferation of weapons of mass destruction ;

b) customer's and transactional related information collected for protecting and controlling anti-money laundering and countering the financing of terrorism.

3/ Financial institutions and designated non-financial businesses and professions should promptly inform the Centre of any customers and transactions that are reasonably suspected to be related to the proliferation of weapons of mass destruction.

4/ The Centre may order the freezing of any funds, economic resources or other assets of a transaction reported to it in accordance with Sub article (3) of this Article for a maximum of 10 days and promptly report such action to the Federal Attorney General.

5/ The Federal Attorney General shall as appropriate institute to the Federal High Court for confirmation and extension of freezing within the period indicated in Sub article (4) of this Article.

## 11. <u>Funds, Other Assets or Economic Resources that Enjoy Exemption from Freezing</u>

The following funds, other assets or economic resources may enjoy exemption from freezing:

1/ Rent or mortgage, salaries, taxes, insurance premiums, public utility charges or professional fees for legal services.

2/ Funds, other assets or economic resources acquired by third parties acting in good faith.

3/ Professional fees of an Administrator or Auditor;

www.chilot.me



፬/ ማዕከሉ በተሰየመው ሰው ማመልከቻ መሰረት እና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ደህንነት ካውንስል በሚሰጠው ስልጣን አማካኝነት መሰረታዊና ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎችን እንዲሁም ከፍረጃ ምዝገባው በፊት ያሉ ከውል የሚመነጩ ክፍያዎች ከእግድ ነፃ እንዲሆኑ ሊያዝ ይችላል፡፡

4/ The Centre may up on the application of designated person and receipt of the authorization of United Nation Security Council expand exemption freezing to basic and extra ordinary expenses as well as payments due under contracts entered into prior to the listing of persons.

**፲፪. <u>የተለየን የገንዘብና የንብረት ቁጥጥሮችና ማዕቀቦችን ስለማንሳት</u>**

፩/ ከዚህ አዋጅ ወይም የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ብዜትን ከመከላከልና ከመቆጣጠር አንጻር አግባብነት ካላቸው ሌሎች ህጎች እንዲሁም ከጉዳዩ አንጻር ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ሥምምነቶች የገባቻቸውን ግዴታዎች በማይጻረር መልኩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ (፩) መሰረት የወሰነውን ውሳኔ ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል፡፡

፪/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ሲወስን ውሳኔው እገዳው ወይም ክልከላው ስለሚነሳበት ሁኔታ ዝርዝር መያዝ ያለበት ሲሆን፣ ሰፊ ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በሚወሰነው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን በተመለከተ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ (፩) እና (፪) መሰረት የተደረገ እገዳና ክልከላ ቀሪ ይሆናል፡፡

**12. <u>Removal of Targeted Financial and Asset Control and Sanctions</u>**

1/ The Council of Ministers may issue a decision to modify or rescind any decision issued pursuant to Article 9 (1) of this proclamation provided that it shall not be contradictory to Ethiopia's obligation provided under this or related other proclamations framed to fight proliferation of weapons of mass destruction and to Ethiopia's obligation under International obligations proper to the issue.

2/ Where the Council of Ministers decides as per Sub-article (1) of this Article, it shall define the terms and conditions applicable to the unfreezing or ending of the prohibition, and cause its order to be published in newspaper having wide circulation.

3/ The freezing actions and prohibitions provided under Article 9 (1) and (2) of this proclamation shall be terminated with respect to those persons subject to a Council of Ministers decision pursuant to Sub-article (1) of this Article.

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## <u>PART FOUR</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**፲፫. <u>ቅጣት</u>**

፩/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፰፣ እና ፱(፭) የተላለፈ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም እስከ ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፪ የዚህን አዋጅ አንቀፅ ፲(፩) እና (፫) የተላለፈ ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው እስከ አስራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና እስከ ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

**13. <u>Penalty</u>**

1/ Any physical person in violation of the provisions of Articles 8 and 9(5) of this proclamation shall be punishable by rigorous imprisonment up to Fifteen years or with a fine not exceeding 1,000,000(one Million Ethiopian birr) or both.

2/ Any physical person in violation of the provisions of Articles 10 (1) and (3) of this proclamation shall be punishable by rigorous imprisonment up to Fifteen years or with a fine not exceeding 1,000,000(one Million Ethiopian birr) or both

www.chilot.me



፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለጸው ወንጀል የተፈጸመው በሕግ ሰውነት በተሰጠው አካል በሆነ ጊዜ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ ፭ሚሊዮን እስከ ፲ሚሊዮን (አምስት ሚሊዮን እስከ አስር ሚሊዮን ብር) በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

## ፲፬. የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት

፩/ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ለማዕከሉ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት ለዚህም አዋጅ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ በወንጀል ተግባር የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፯፻፹/፪ሺ፭ ያሉ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ለዚህም አዋጅ ተፈፃሚ ናቸው፡፡

፫/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፪/፪ሺ፩፣ አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሕጎች ስለምርመራ፣ ገንዘብ ወይም ንብረት ስለመያዝ፣ ንብረት ስለማስተዳደር፣ ስለመውረስ፣ ስለ ተያያዥ ወንጀሎች እና ስለዓለም አቀፍ ትብብር የተመለከቱ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ለዚህም አዋጅ ተፈፃሚ ናቸው፡፡

## ፲፭. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ኮሚቴው ይህን አዋጅ እና በንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወጣ ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፮. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ሚያዚያ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3/ Where the offence under Sub article (1) and (2) of this Article has been committed by a juridical person, in addition to Administrative measures it shall be punishable with a fine of 5,000,000-10,000,000 ( five Million to Ten Million Ethiopian birr.)

## 14. Applicability of Other Laws

1/ The powers and duties entrusted to the Centre by relevant laws shall also apply to this Proclamation.

2/ The relevant provisions of the prevention and suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism Proclamation No. 780/2013 shall apply to this Proclamation.

3/ The relevant provisions of Proclamation No. 652/2009, Proclamation No. 881/2015 and other laws regarding investigation, freezing, asset management, confiscation, ancillary offence, and international cooperation shall apply, to this Proclamation.

## 15. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Committee may issue Directives necessary for the proper implementation of this Proclamation and Regulations issued under Sub article (1) of this Article.

## 16. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 19th day of April, 2019.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me